የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፱
አዲስ አበባ–ታኅሣሥ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8[th] Year No. 9
ADDIS ABABA–3[rd] January, 2002


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፫/፲፱፻፺፬ ዓ·ም
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዕረፍትና የሥራ ጊዜ (ማሻሻያ) አዋጅ ........................................ ገጽ ፩ሺ፮፻፸፰


CONTENTS


Proclamation No. 263/2002
Recess and Time-in-Session of the House of Peoples' Representatives (Amendment) Proclamation ........................................ Page 1678


## አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፫/፲፱፻፺፬
## የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን የዕረፍትና የሥራ ጊዜ ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዕረፍትና የሥራ ጊዜን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና ፶፰ (፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዕረፍትና የሥራ ጊዜ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፫/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ማሻሻያ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዕረፍትና የሥራ ጊዜን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፪/፲፱፻፹፰ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩· የአዋጁ አንቀጽ ፪ እንደሚከተለው ተሻሽሏል ፤

## *PROCLAMATION NO. 263/2002*
## *A PROCLAMATION TO AMEND THE RECESS AND TIME-IN-SESSION PROCLAMATION OF THE HOUSE OF PEOPLES' REPRESENTATIVES*

WHEREAS, it has become necessary to amend the recess and time-in-Session Proclamation of the House of Peoples' Representatives;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and 58(2) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Recess and Time-in-Session of the House of Peoples' Representatives (Amendment) Proclamation No. 263/2002."

2. *Amendment*

The Recess and Time-in-session of the House of Peoples' Representatives Proclamation No. 32/1996 is amended as follows:

1/ Article 2 of the Proclamation is amended as follows:

፪· <u>የዕረፍት ጊዜ</u>

"የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዕረፍት ጊዜ በየዓመቱ ከየካቲት ፩ እስከ የካቲት ፴ እና ከሐምሌ ፩ እስከ መስከረም ወር የመጨረሻ ሳምንት ሰኞ ዋዜማ ድረስ ይሆናል።"

፪· የአዋጁ አንቀጽ ፫ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፫· <u>የሥራ ጊዜ</u>

"የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሥራ ጊዜ በየዓመቱ ከመስከረም ወር የመጨረሻ ሳምንት ሰኞ እስከ ጥር ፴ እና ከመጋቢት ፩ እስከ ሰኔ ፴ ድረስ ይሆናል።"

፫· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከታኅሣሥ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም

ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. **Recess**

"The annual recess of the House of Peoples' Representatives shall be from the 1st day of Yekatit (8th of February) to the 30th day of Yekatit (9th of March) and from the 1st day of Hamle (8th of July) to the eve of Monday of the final week of the month of Meskerem (September)."

2. Article 3 of the Proclamation is amended as follows:

3. Time-in-Session

"The annual time-in-session of the House of People's Representatives shall be from Monday of the final week of the month of Meskerem (September) to the 30th day of Tir (7th of February) and from the 1st day of Megabit (10th of March) to the 30th day of Sene (7th of July)."

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 3rd day of January, 2002.

Done at Addis Ababa, this 3rd day of January, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE